# ይድረስ ለወንድም ጋሻ

ደግሞ ተራብክ ይበሉኝ ዛሬም?
ከትናንቱ መቅሰፍት ሳታገግም።
ምነዋ አንተ ባቴሌ፣ ምነዋ ወንድም ጋሻ፣
ልቡቃያህ አጣህለት የለት ጉርሻ።
አይጠፉኝም የራብ ሹል ብረት
ዘልዝሎ ይከታትፉል፣ አንጀት፣
ሆድ እቃቸው የደረቀ ሚያጣጥሩ ሕጻናት፣
ጨንራ ይመስል፣ ፊታቸውን በዝንብ የተቀሙ
የድረሱልን ጥሪ ሊያስተጋቡ ዓይኖቻቸውን አስለመለሙ።
ወንድም ጋሻ በተሌቭዥን ብቅ አሉ ልጆችህ ዛሬም
ምጽአት ሆነ፣ ሕጻን ልጅ ከራብ ጋር አይካረም።

አፍ ሳልፈታ ቀርቶ፣ ራብ ሳዋቂ ፋታ አይሰጥ
አንዣበበ ጆቢራው፣ ያልደረሰ ሕጻን አንጀት ሊመዠርጥ
በዚያን በኩንቢው ያይኖቹን ብረት ሊያፈርጥ፣ ሊደፈጥጥ።
የተራበ፣ የተጠማ ጉሮሮውን ሊቆፍር፣ ቆሚል ሰልፍ
የተሚጠጠ የሆድ ዕቃ ሊዘረግፍ፣
በዚያን ረዣዥም ጥፍር፣ የሞት ጅራፍ፣ሊጋረፍ።
አክናፋቱን እያማታ ይጠባበቃል ያንተን ጣር
አወይ ያንተ እስትንፋስ ሲቆም፣ ሕይዎት ሲከር
በቁም የሕጻን ሬሳ ነው መከር።

እኔማ አጠገብህ የለሁ፣ እንዳላዳምጥ ያንተን ማቃሰት የልብ ትርታ
ብቼኝነት ውስጥ ተደብቄ ባይነ ስጋ እንኳ ላንገናኝ ላፍታ
የቁም ሙት እንከላወሳለሁ በውርደት ወጥቼ ከሰው ተርታ።
ያባት ዕዳ ተሸክሜ ሰው አገር እንከራተታለሁ
ላትወጣልኝ፣ ላልገላገልህ የጽንስ ሽል ተሸክሜ እማስናለሁ።
በኢትዮጵያ አምላክ ይሁንብህ ወንድም ጋሻ አትፍረድብኝ
አንተን ሆድህን፣ እኔን ሂሊናዬን ራበኝ።

ከቶ ሳልጠይቅህ፣ መቻል ውሻህስ እንዴት ነው፣
ለርሱስ ማን ደረሰለት የለት ጉርሱ አኮ እጅህ ነው።
ቀዬህ ቆለ ርቆት ማጀትህ ከነጠፈ
ውርዬም ተራበችብህ፣ አንጀትዋ ተጣበቀ፣ ካንጀቱ ተለጠፈ።
መቻል ቡችሎቹን አስከትሎ በራብ ሲያላዝን
ያቺን የቢችሎቹን እናት ችሎ ማደረን
ራብ ጠናባት አሉ የማሪያም አራስዋን፣
ዋልኝ! እመጫትዋን።

ውሮ የወተት ከልዋ፣ ደርቆ፣ ነጥፎ፣ ርቆት አዋይ፣
ሚያው ስትል አደረች እጅ እጅህን ስታይ
ግልገሎችዋም ከስርዋ ድክ ድክ ዋ---ይ     ዋ------ ይ   ----
ኸረ ጨከነ ፈጣሪ አመረረ ሰማይ
ወንድም ጋሻዬ በምንህ ቻልከው፣ ይህን የምድር ላይ ሰቆቃ ስቃይ።
ሰውማ ቁጣ ነው ተባለ፣ የነፍስ አባት ገዘቱና

የቤት እንስሳቱን በራብ ይቀጣል ምነው ጌታ፣ ምን አጠፉና?
አንተማ ለራብ እጅ ከሰጠህ ምድሩን ካስደፋህ አንገት
ችግር ገጥሞሃል ማለት ነው፣ አደባባይ መውጣት ያለበት
ቡሄ እኮ ደረሰ ሆ ብለን መጣን ሊሉ ነው ሕጻናት::
ያስለመድከውን ሙልሙል ዳቦ ለሰፈሩ ሕጻን
ቡሄ ቡሄ ስላቦ ትኩሱን ዳቦ እየተባልክ፣ ብታዞር ፊትህን
እነርሱ አይረዱም ራብ ጥማትህን
ማጹ ተሰልቦ የመሶቡን ድር ማዳር አያቅልህ ሕጻን::

ዝናብ ጠፍቶ ነው በሚልማ አትስጥ ምክንያት
ለም ነው መሬቱ፣ ለመስኖ መጥለፍ ተሳነህ ጅረት፣
ዳኑ እኔም ፍርደ ገምድል እይደለሁም፣ ባንተ አልፈርድም
ፊደል ያስቆጠርከው፣ ጥበብ ሳያሳይህ ጎንህ ሳይቆም::
ሆኖም የፈጣሪ ቁጣም ነው፣ አይባል ነገር
እንደ ኢትዮጵያ እጁን የዘረጋ አላየሁም አገር::
አላላውስ ብሎህ እንደሆ የተፈራረቀብህ መስተዳድር
በቃኝ በላቸው፣ ልጆችህ ናቸውና ያስተማርካቸው ሳትማር::

ለዘመናት ያለህበትን መለወጥ ተስኖህ
ብልጭ ድርግም በሚል ዝናም ተማምነህ
ሁሌም በክስተት መመራቱ ስለማያዛልቅህ፣
በኔ ይሁንብህ፣ ወንድም ጋሻ መስኖ ቦይ ቅደድ
በደጅህ ለሚፈልቅ ሀብት አያሻህም ፈቃድ::

በስንዴ እርዳታ፣ ጥሬ በቁና እየተሰፈረልህ
መቼ ድረስ ይዘለቃል፣ በውርደት አንገት ደፍተህ?
እነርሱማ ምን አለባቸው፣ ስንዴ በቁና ሰፋሪዎቹ
ይቡቃዮችህን የራብ ሳል ጠኔ እያሳዩ ለተመልካቹ፣
አለም አቀፍና አገር በቀል ቢሮ ከፍተው
ባንተ ሕይዎት ይነግዳሉ፣ እነርሱ ኪሳቸውን አሳብጠው::
ሲላቸው የሙዚቃ ድግስ ያዘጋጁና
ያንተን የወንድም ጋሻን የጠወለገ ገላ እያሳዩ አለም መዲና
ዶላሩን ይቀራመታሉ፣ ፊደል ካስቆጠርከው ይመሳጠሩና::

ለምድር አታስብ ሰማይ ነውና ቤትህ
የሚሉህን እትስማ፣ ለራብህ አይቆሙም ጎንህ::
በስምህ አደባባይ ይጠራራሉ፣ እነርሱም ምጽዋእት ይሰበስባሉ፣
ገንዘቡን ኪሳቸው፣ ላንተ ጸሎት በመንፈስ ይልካሉ
አምላኬ ሆይ ኢትዮጵያን ጠብቃት እያሉ::
ዶላር እንጂ ጸሎት ዳቦ ላይገዛ
ወገን ባንተ ስም ነገደ ወንድም ጋሻ፣ ያንተ መኖር ቀርዝዛ
ነፍስ በየጥሻው እየወደቀ እንደ ዋዛ::
አንተ ብቻ ጥረህ ተጣጥረህ፣ በግርህ ቁምልኝ ወንድም ጋሼ
ራብ በስራ ይዳኛል፣ስምም ይነጻል እይቀር እንደተበላሸ::

ተሻለ ሀ/ማሪያም
ስኮትላንድ